# የኩፍኝ በሽታ (ሩቤላ)

## የኩፍኝ በሽታ ምንድን ነው?

ኩፍኝ፣ እንዲሁም ሩቤላ ተብሎ ይጠራል፣ በቫይረስ የሚከሰት በጣም የሚተላለፍ በሽታ ነው። ከፍተኛ የክትባት መጠን በመኖሩ ከእንግዲህ ኩፍኝ በዩናይትድ ስቴትስ የተለመደ አይሆንም። ነገር ግን አሁንም በሌሎች ብዙ አገሮች የተለመደ ሲሆን ባልተከተቡ ተጓዦች ምክንያት ወደ U.S. ሊመጣ ይችላል። የኩፍኝ በሽታ ወረርሺኞችን ለመከላከል የኩፍኝ ክትባት መጠኖችን ከፍ ማድረግ ወሳኝ ነው።

## የኩፍኝ በሽታ ምልከቶች ምንድ ናቸው?

- ሽፍታ እና
- ትኩሳት እና
- ሳል ወይም በፈሳሽ የተሞላን አፍንጫ ወይም የደብዘዝ ያሉ አይኖች

አንድ ሰው ለኩፍኝ በሽታ ከተጋለጠ በኋላ ከስምንት እስከ 12 ቀናት ውስጥ የበሽታ ምልክቶች ይታያሉ። አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያው የበሽታ ምልክት ትኩሳት ነው። ሽፍታው አብዛኛውን ጊዜ ትኩሳቱ በጀመረ ከ 2 እስከ 3 ቀናት ውስጥ የሚታይ ሲሆን ከ 5 እስከ 6 ቀናት ይቆያል። ሽፍታው ከጸጉር ስር ጀምሮ፣ ወደ ፊት እና ወደ ላይኛው አንገት ይሄዳል ከዚያም ወደሰውነት ይወርዳል።

## እርስዎ ወይም ልጅዎ የኩፍኝ በሽታ ምልክቶች ካለባችሁ ምን ሊያደርጉ ይገባል?

ከሐኪምዎ ወይም ከክሊኒክዎ ጋር እስከሚነጋገሩ ድረስ ቤት ውስጥ ይቆዩ እንድሁም ጎብኝዎችን ከመቀበል ይቆጠቡ። ለጉብኘት መምጣት ካለብዎት ሃኪምዎ ወይም ክሊኒክዎ ይነግርዎታል።

## የኩፍኝ በሽታ ምን ያህል ከባድ ነው?

ኩፍኝ ሆስፒታል ተኝቶ መታከም አልፎ ተርፎም ሞት ሊያስከትል የሚችል ከባድ በሽታ ነው። የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ብዙ ሰዎች እንደ ተቅማጥ፣ የጆሮ ኢንፌክሽኖች፣ የሳንባ ምች ወይም ሃይለኛ የአንጎል ብግነት (ዘላቂ የአእምሮ ጉዳት የሚያስከትል የአዕምሮ ኢንፌክሽን ችግር ይኖራቸዋል)። ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት እና ዕድሜያቸው ከ 20 አመት በላይ በሆኑ አዋቂዎች ላይ ህመሞች ይበልጥ የተለመዱ ናቸው።

በእርግዝና ወቅት የሚመጣ የኩፍኝ በሽታ ያለጊዜው ለሚመጣ ምጥ፣ ለጽንስ መጨንገፍ እና ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ሕጻናት ለመውለድ የመጋለጥ አደጋን ይጨምራል። በተለይ የኩፍኝ በሽታ የሰውነት የበሽታ ተከላካይ ስርዓታቸው ደካማ በሆኑ ሰዎች ላይ ከባድ ሊሆን ይችላል።

## የኩፍኝ በሽታ እንዴት ይዛመታል?

የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ሲተነፍሱ እና ሲያስሉ በአየር አማካኝነት ይዛመታል። በጣም ተላላፊ ነው። የኩፍኝ በሽታ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊይዝዎት አይችልም፣ ምክያቱም ከያዝዎት በኋላ፣ በሽታውን የመከላከል አቅም ይኖርዎታል።

## የኩፍኝ በሽታ ያለበት ሰው ለምን ያህል ጊዜ አስተላላፊ ይሆናል?

የኩፍኝ በሽታ ያለበት ሰው ሽፍታው ከመታየቱ ከ 4 ቀናት በፊት ጀምሮ እንድሁም ሽፍታው ከታየ ከ 4 ቀናት በኋላ ለሌሎች ሊያስተላልፍ ይችላል።

# ለኩፍኝ በሽታ ህክምና አለው?

አይ፣ ለኩፍኝ በሽታ ምንም የተለየ ህክምና የለም። የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች አልጋ ላይ እረፍት ማድረግ፣ ፈሳሾች እና ትኩሳትን መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። እንዲሁም እንደ ተቅማጥ፣ የጆሮ ኢንፌክሽን ወይም የሳንባ ምች ላሉ ህመሞች ህክምና ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

# ለኩፍኝ በሽታ ክትባት አለ?

አዎ። አብዛኛውን ጊዜ የኩፍኝ ክትባቱ ከጆሮ ደግፍ በሽታእና ከጀርመን ኩፍኝ (MMR) ጋር ይተዋሃደ ነው።

- ልጆች ዕድሜያቸው ከ12-15 ወራት ሲሆን እና ከ 4-6 አመት ሲሆናቸው የ MMR ዶዞችን ያገኛሉ፤ ሁለተኛው MMR ከመጀመሪያው ዶዝ አንድ ወር በኋላ ወዲያውኑ ሊሰጥ ይችላል።
- አለም አቀፍ ጉዞ ለሚያደርጉ ወይም ወረርሽኙ በሚከሰትባቸው በታዎች ለሚሄዱ ዕድሜያቸው ከ 6-12 ወር ለሆኑ ህጻናት የ MMR የመጀመሪያ ዶዝ ይመከራል።
- ኩፍኝ ይዟቸው የማያውቅ ወይም የኩፍኝ ክትባት ያልወሰዱ አዋቂዎች በተለይም 1957 ወይም ከዚያ በኋላ የተወለዱ ከሆኑ አንድ ዶዝ የ MMR ክትባት ሊወስዱ ይገባል።
- ተማሪዎች (የኮሌጅ ተማሪዎችን ጨምሮ)፣ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች እና አለም አቀፍ ተጓዦች ሁለት ዶዝ የ MMR ክትባት መውሰድ አለባቸው፣ ካልተከተቡ፣ ሊከተቡ ይገባል።
- እርስዎ ወይም ልጅዎ ምን አይነት ክትባቶች እንደሚያስፈልጋችሁ ጥያቄዎች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

# እርስዎ ወይም ልጅዎ ለኩፍኝ በሽታ ከተጋለጡ ምን ሊያደርጉ ይገባል?

- ወዲያውኑ ለሃኪምዎ ወይም ለክሊኒክዎ ይደውሉ። ለጉብኝት መምጣት ካለብዎት የሚያሳውቁዎት ይሆናል።
- ካልተከተቡ፣ ከተጋለጡ በኋላ ባሉት 3 ቀናት ውስጥ የ MMR  ክትባት መውሰድ በኩፍኝ ከመያዝ ሊከላከላቸው ይችላል።
- ለኩፍኝ በሽታ በተጋለጡ በ 6 ቀናት ውስጥ ኢሚውኖ ግሎቡሊን (ለኩፍኝ ቫይረስ ጸረ እንግዳ አካላት ያለው የደም ምርት) ክትባት ከወሰዱ፣ የኩፍኝ በሽታን ሊከላከል ወይም ሃይለኛነቱን ሊቀንስ ይችላል።

# በትምህርት ቤት ወይም በሌላ ቦታ (ለምሳሌ:- የበጋ ዘመቻ፣ የህጻናት እንክብካቤ፣ የስራ ቦታ፣ ክሊኒክ)  የኩፍኝ በሽታ ከተገኘስ?

MDH እና የአካባቢ ጤና መምሪያዎች የተጋለጡትን ግለሰቦች ለመለየት፣ ለኩፍኝ በሽታ ያላቸውን የመከላከል አቅም ለመገምገም እና ለዚያ የተለየ ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ ከድህረ ተጋላጭነት መከላከያ ለመምከር ከአካባቢው ጋር ይሰራሉ።

Minnesota Department of Health
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
[www.health.state.mn.us/measles](http://www.health.state.mn.us/measles)

07/01/2017

*ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት በሚከተለው ላይ ይደውሉ:- 651-201-5414።.*